# Ideas to Action

**PARTICIPANT WORKBOOK**





CENTER FOR ENVIRONMENTAL HEALTH EQUITY
UNIVERSITY *of* WASHINGTON

# ዕውቅናዎች እና ምስጋና

University of Washington Center for Environmental Health Equity (UW CEHE, የዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጤና ፍትሃዊነት ማዕከል) የሚገኘው በUniversity of Washington የሲያትል ካምፓስ ውስጥ ነው እንዲሁም የዚያ ምድር የባህር ዳርቻ ሳልሽ ህዝብ፣ የዱዋሚሽ፣ ሱኳሚሽ፣ ቱላሊፕ እና ሙክለሾት ብሄሮችን ጨምሮ የሁሉንም ጎሳዎች እና ባንዶችን የጋራ ውሃ ለሚነካ መሬት እውቅና እንሰጣለን።

ተወላጆችን ከይዞታቸው ማፈናቀልን እና በግዳጅ ማፈናቀልን ጨምሮ የዩናይትድ ስቴትስ የፌዴራል እና የግዛት መንግስታት ላደረጓቸው ያልተሳኩ ሙከራዎች ዕውቅና በመስጠት ከጎሳዎች እና የጎሳ ማህበረሰቦች ጋር በምናደርገው አጋርነት ይህን ስህተት ለማስተካከል እና አቅምን ለመገንባት እንዲሁም ከመሬታቸው ጋር ያላቸውን ሉዓላዊ ግንኙነት በማደስ ይህን ስህተት ለማስተካከል እንጥራለን።

ለOne Roof Foundation (ዋን ሩፍ ፋውንዴሽን) ለተሸላሚ ጸሐፊዎች ላደረጉት ድጋፍ እና በDepartment of Commerce (የንግድ ዲፓርትመንት) እና Hagerty Consulting ላሉት አጋሮቻችን ጥልቅ ምስጋና ልናቀርብ እንወዳለን።
በመጨረሻም ከማዕከላችን ጋር ተሳትፎ ለማድረግ እና ሥራቸው እና የማወቅ ጉጉታቸው የዚህን አውደ ጥናት ይዘት ያነሳሱ ማህበረሰቦችን እና ጎሳዎችን እናመሰግናለን።

# ስለዚህ አውደ-ጥናት እና የሥራ መጽሐፍ

የዚህ አውደ-ጥናት ዓላማ **ለማህበረሰብዎ ለአካባቢያዊ የፍትህ ፕሮጀክት ገለፃን በመገንባት ላይ እርስዎን ለመደገፍ** ወይም ከሀሳቦች ወደ ትግበራ ለመሄድ ነው። በአውደ-ጥናቱ ወቅት፣ ይህ ፕሮጀክት ምን ሊመስል እንደሚችል እና ለውጭ ታዳሚዎች እንዴት ማስተላለፍ እንደሚችሉ እንዲያስቡ ወደሚያግዙዎት ተከታታይ ልምምዶች እና እንቅስቃሴዎች እንመራዎታለን።

ለአውደ-ጥናቱ ይህን የሥራ መጽሐፍ እንጠቀማለን። በሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ልምምዶች እና እንቅስቃሴዎች ማጠናቀቅ ሃሳቦችዎን እና የፕሮጀክት ሃሳቦችን ለማደራጀት እና ለፕሮጀክት ፕሮፖዛል ሃሳብዎን ለማስተላለፍ የሚያግዝበት አንዱ መንገድ ነው።
እያንዳንዱ የሥራ መጽሐፍ ክፍል ከተለመደ የስጦታ ማመልከቻ ክፍል ጋር ይገናኛል፡-

| **የሥራ መጽሐፍ ክፍል(ሎች)** | **የተለመደ የስጦታ ማመልከቻ ክፍል** |
|---|---|
| ድርጅትዎን በማወቅ ላይ | የድርጅት ዳራ<br>የማህበረሰብ መግለጫ |
| ከአካባቢያዊ ፍትሕ ጋር ይህን ማገናኘት | የማህበረሰብ መግለጫ<br>የፍላጎት መግለጫ ወይም የችግር ገለጻ |
| የእርስዎን “ምን” እና “ለምን” ስም መስጠት | የፍላጎት መግለጫ ወይም የችግር ገለጻ |
| የአመክንዮ ሞዴል | የፕሮጀክት መግለጫ ወይም የፕሮጀክት ትረካ<br>የግምገማ ወይም የልኬት ስኬት |

የአውደ-ጥናቱ አስተናጋጆች በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ላይ ሥራዎን ያበረታታሉ። ይህ የሥራ መጽሐፍ ሀሳቦችዎን በጋራ ለመሰብሰብ እንዲያግዙ ጥያቄዎችን እና መመሪያዎችን ያቀርብልዎታል። የራስዎን ሀሳቦች ለማደራጀት በሥራ መጽሐፍ ውስጥ ለመፃፍ ነፃነት ይሰማዎት፣ የተተየቡ ማስታወሻዎችን ለመውሰድ ተጓዳኝ ዲጂታል ረቂቅም ይቀርባል

# ማውጫ

ስለዚህ አውደ-ጥናት እና የሥራ መጽሐፍ ........ 3
ለእርስ በእርስ የሚሆኑ የሚጠበቁ ነገሮች ........ 5
ታሪክዎን መናገር ........ 6
ከአካባቢያዊ ፍትሕ ጋር ይህን ማገናኘት ........ 8
የእርስዎን “ምን” እና “ለምን” ስም መስጠት ........ 9
የአመክንዮ ሞዴል ........ 13
ለቀጣይ እርምጃዎች የሚሆኑ መርጃዎች ........ 16
የግምገማ ፈንድ ማድረግ ማሳወቂያዎች መሣሪያ ........ 17
ስለ UW CEHE ........ 19

# ለእርስ በእርስ የሚሆኑ የሚጠበቁ ነገሮች

እባክዎ እነዚህ ነገሮች እንዴት አብረን እንደምንሰራ ውይይት ለማድረግ የሚሆን የመጀመሪያ ቦታ መሆናቸውን ልብ ይበሉ። እንደ አስፈላጊነቱ ስለ እነዚህ የምንወያይበት እና የምናዘምንበት ዕድል ይኖረናል።

1. **W.A.I.T.፦ "ለምንድን ነው የማወራው?" ወይም "ለምንድን ነው የማላወራው?"**
2. **ታሪኮች ይቆያሉ፣ ትምህርቶች ይሄዳሉ**
3. **"ወይኔ፣" "ውይ"፦ ሀሳብን ይመኑ፣ ተጽዕኖ ላይ ባለቤት ይሁኑ**
4. **ለመረዳት ቀላል እንዲሆን አድርገው ይናገሩ፣ ለመረዳት ያዳምጡ**
5. **ሰዎች በራሳቸው ተሞክሮዎች ውስጥ ባለሙያዎች ናቸው**

እነዚህ ተስፋዎች የተመሰረቱት ከJemez Principles for Democratic Organizing እና ከDefend the Sacred Alaska Principles የተጠበቁትን የAlaska Just Transition Summit ላይ ነው።

**ከእነዚህ የሚጠበቁ ነገሮች የሚጎድል ነገር አለ? ከቡድኑ ጋር የሚጋራ የዲጂታል የሥራ መጽሐፍዎ ውስጥ ማስታወሻዎችን ይውሰዱ።**

የእነዚህ ሁሉ የሚጠበቁ ነገሮች ማዕከል ላይ አንዱ ለሌላው የሚኖረው ክብር እና የምናመጣቸው ግለሰባዊ ልምዶች እና ስጦታዎች ነው። አንድ ሰው እነዚህን የሚጠበቁ ነገሮች እንደማይከተላቸው ከተሰማዎት የUW CEHE ቡድን አባል፣ በጎ ፈቃደኛ ወይም የአውደ-ጥናት ተሳታፊ ቢሆኑ እባክዎ ለአውደ ጥናቱ አስተባባሪዎች ያሳውቁ እና እኛ እንዴት ልንፈታው እንደምንፈልግ አንድ ላይ እቅድ እናወጣለን።

# ታሪክዎን መናገር

ብዙውን ጊዜ፣ የስጦታ ፕሮፖዛሎች የግል እና ድርጅታዊ ጥንካሬዎችዎን እና ልምድዎን እንዲለዩ እና እንዲሰይሙ ይጠይቁዎታል። ብዙ ሰዎች ሊያጋሩት የሚችሉት ብዙ ተሞክሮ እና ጥበብ ቢኖራቸውም፣ ይህ ሊያስፈራ ወይም እንደ ጉራ ሊሰማቸው ይችላል። እርስዎን እና ድርጅትዎን ቀደም ብለው ለሰሩት ስራ እና ላመጡት እውቀት እንዲያንጸባርቁ ለመርዳት፣ የእኛን ግላዊ እና ድርጅታዊ ታሪኮችን ለመለዋወጥ የትረካ መንገድን እንጠቀማለን።

ስለ *ሥራዎ* እና እይታዎ በማጋራት ላይ እርስዎን ለመምራት እንዲያግዙዎት ተከታታይ ጥያቄዎች ይጠየቃሉ። የዚህ ውይይት አንዳንድ ገጽታዎች ለእርስዎ ጠቃሚ የሆኑ እና ለምን ይህን ስራ እንደሚሰሩ ላይ ያሉ ልምዶች፣ ፍራቻዎች፣ ተስፋዎች እና ታሪኮች ይሆናሉ። እንደ አውደ ጥናቱ አንድ አካል፣ እነዚህ ታሪኮች ተዘጋጅተው በፈለጉት መንገድ እንዲጠቀሙ ተደርገው ይመለሳሉ - ለምሳሌ፣ በድረ-ገጽዎ፣ በማህበራዊ ድህረ-ገጾችዎ ላይ ወይም በስጦታ ማመልከቻ ላይ ይጣጣማሉ።

<u>የእርስዎን ፕሮፋይል/*መግለጫ ማጋራት ሙሉ በሙሉ አማራጭ ነው እና ፎቶዎን እና/ወይም ቃላትዎን እንድናጋራ የማይፈልጉ ከሆነ ያለፈቃድዎ አናደርገውም።*</u>

በጠረጴዛዎ ላይ የሚከተሉትን የመግቢያ ጥያቄዎች እና በጥያቄ ባንክ ውስጥ ካሉት ምድቦች ቢያንስ አንዱን ይመልሱ። ማስታወሻዎችን ለመውሰድ የእርስዎን ዲጂታል የ*ሥራ* መጽሐፍ ይጠቀሙ።

**የማስተዋወቂያ ጥያቄዎች፡-**

1. *ማህበረሰብዎን ያስተዋውቁ* – አምስቱን ስሜቶች በመጠቀም ማህበረሰብዎን መግለጽን ከግምት ውስጥ ያስገቡ (ምሳሌ.. *ማህበረሰብዎ ሲነገርለት ምን ይመስላል? ሲታይ ምን ይመስላል? በማህበረሰብዎ ውስጥ መሆን ምን ዓይነት ስሜት አለው? ምን ዓይነት ጣዕሞች ወይም ሽታዎች ማህበረሰብዎን ያስታውሱዎታል?*)
2. ድርጅትዎን ወይም ጉሳዎን ያስተዋውቁ – የእርስዎ ተልዕኮ እና ዕይታ ምንድን ነው? ድርጅትዎ ምን ያደርጋል? የሚያገለግሉት ማንን ነው?
3. *ራስዎን ያስተዋውቁ* – ማን ነዎት? ሚናዎ ምንድን ነው? ለምን ያህል ጊዜ ሲያደርጉት ነበር?

**የጥያቄ ስብስብ (ከእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ቢያንስ አንዱን ለመመለስ ይምረጡ!)፡-**
*ስለ ማህበረሰብዎ ያሉ ጥያቄዎች፡-*

1. በጥልቅ የሚጨነቁለት የማህበረሰብዎ አካል ምንድን ነው?
2. ስለ ማህበረሰብዎ በጣም ተስፋ የጣሉበት አንድ ነገር ምንድን ነው?

ስለ ድርጅትዎ ወይም ጎሳዎ ያሉ ጥያቄዎች፡-

1. የድርጅትዎ ወይም ጎሳዎ የሚያኮራ አፍታ ምንድን ነው?
2. ድርጅትዎ ወይም ጎሳዎ በጣም ጥንካሬ የተሰማቸው ወይም ጠንካራ ጊዜ ያሳለፉበትን ጊዜ ታሪክ ማጋራት ይችላሉ?

*ስለ እርስዎ ያሉ ጥያቄዎች፡-*

1. ከማህበረሰቡ ጋር ላለዎት *ሥራዎ* የሚስብዎት ነገር ምንድን ነው?
2. ወደ *ሥራዎ* የሚያመጡት የእርስዎ የተደበቀ ችሎታ ወይም ልዩ ክህሎት ምንድን ነው?

3. በጣም የጓጉለት ነገር ምንድን ነው?
4. የሚበለጽግ ማህበረሰብን ለመፍጠር በህይወትዎ ውስጥ በጣም የሚያነሳሳዎት ማን ነው? ለእነሱ ስላለዎት ተስፋዎች ይንገሩን።

# ከአካባቢያዊ ፍትሕ ጋር ይህን ማገናኘት

*ሥራዎ ከትልቁ የአካባቢ የፍትሕ እንቅስቃሴ ጋር እንዴት ይገናኛል? የአካባቢ ፍትህ ለእርስዎ ምን ማለት እንደሆነ እና ሥራዎ ለማህበረሰብዎ የአካባቢ ፍትህን እንዴት ሲደግፍ እንደሚመለከቱ ለማየት ትንሽ ጊዜ እንወስዳለን። እነዚህን ነጥቦች ማገናኘት ሌሎችን ለማምጣት፣ አፍታን ለመገንባት እና ሥራዎን ለመደገፍ የሚያስችሉ ግብዓቶችን ለመለየት ይረዳዎታል።*

በጠረጴዛዎ ላይ ካሉ ሰዎች ጋር ውይይትን ለመምራት ጥያቄዎቹን ይጠቀሙ። አስፈላጊ ከሆነ በዲጂታል የስራ መጽሐፍዎ ላይ ማስታወሻ ለመያዝ ነፃነት ይሰማዎ።

1) የአካባቢ ፍትህ ለእርስዎ እና ለማህበረሰብዎ ምን ማለት ነው?
2) የአካባቢ ፍትህ የሚለውን ቃል ሲሰሙ ወደ አእምሮዎ የሚመጡት የትኞቹ ምስሎች ናቸው?
3) ቤተሰብዎ፣ ማህበረሰብዎ ወይም ባህልዎ ስለ አካባቢ ፍትህ ምን አስተምረዎታል?
4) የአካባቢ ፍትህን በተመለከተ ማህበረሰብዎ ምን ተግዳሮቶች ያጋጥመዋል?
5) የአካባቢ ፍትህን ማግኘት ለማህበረሰብዎ ምን ይመስላል?
6) ድርጅትዎ ለዚህ የአካባቢ ፍትህ ራዕይ እንዴት ነው የሚሰራው?
7) ድርጅትዎ ለዚህ የአካባቢ ፍትህ ራዕይ በምን መንገዶች ይሠራል?

# **የእርስዎን “ምን” እና “ለምን”** ስም መስጠት

ለስጦታ ጽሑፍ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ክህሎቶች አንዱ በማህበረሰብዎ ውስጥ የሚያዩትን ፍላጎት ማብራራት እና ያቀረቡትን የመፍትሄ ሃሳብ መግለጽ ነው።

በዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የእርስዎ ፕሮጀክት ለመፍታት ያሰበውን **ምን** ፍላጎት ወይም ችግር እና ይህ ፍላጎት ወይም ችግር **ለምን** እንደሚገኝ ማንሳት እንጀምራለን። የፍላጎቱን መንስኤ ለማግኘት “ግን ለምን” ልምምድን እንጠቀማለን። እሱን ማስተናገድ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ለመግለጽ “ስለዚህ ምን” ልምምድን እንጠቀማለን።

ከዚህ የረቂቅ ክፍል የሰጧቸው መልሶች ለስጦታ ማመልከቻ “የፍላጎት መግለጫ” ወይም “የችግር መግለጫ” ክፍልን መጠቀም ይችላሉ።

**“ግን ለምን” እንቅስቃሴ፦**

1. በሰንጠረዥዎ የአካባቢ ፍትህ ፕሮጀክትዎ ለመፍታት እየሞከረ ያለውን በማህበረሰብዎ ውስጥ የለዩትን ፍላጎት ያካፍሉ። *ለምሳሌ. "በሰፈራችን ውስጥ መጥፎ የአየር ጥራት አለን።"* በይለጥፉት ማስታወሻ ላይ ይጻፉት እና በዛፍ ምስል ከላይ ያስቀምጡት። ይህ በዛፍዎ ላይ “ኮፈን” ነው

2. አንድ አጋርዎ “ግን ለምን?” እያለ እንዲጠይቅ ያድርጉ እና እንዲመልስ ለማድረግ ይሞክሩ። *ለምሳሌ. "የቀለበት መንገድ በሰፈራችን ውስጥ ያልፋል" ወይም "በሰፈሩ ውስጥ ምንም ዛፎች የሉም።"* ለእያንዳንዱ መልስ በይለጥፉት ማስታወሻ ላይ ይጻፉት። እነዚህ የዛፍዎ ስሮች ናቸው። በተቻለ መጠን ግልጽ ይሁኑ - ለእርስዎ ግልጽ የሚመስለው ነገር ለሌላ ሰው ላይሆን ይችላል!

3. ይህን ለበርካታ ጊዜያት ይደጋግሙ። ለእያንዳንዱ መልስ በይለጥፉት ማስታወሻ ላይ ይጻፉት እና በዛፍ ላይ ያኑሩት። እነዚህ ከዋናዎቹ ሥሮች የሚወጡ ጥልቅ ስሮች ናቸው። መልሶችዎ ይበልጥ ትልቅ እና ሰፊ መሆን ሊጀምርይ ይችላሉ።

   *ለምሳሌ. "የመሬት አጠቃቀም ውሳኔዎች" ወይም "የህዝብ ኢንቨስትመንት እጥረት"*

4. በወረቀት ላይ ሲመለከቱት ፕሮጀክትዎ ለመፍታት የሚሞክረው ምንድን ነው? ይህ በተለምዶ በርካታ ነጥቦች ሊሆን ይችላል። በዛፍዎ ምስል ላይ ያክብቡባቸው እና ከአጋር ጋር ይወያዩ።

   *ለምሳሌ. አስቀድሞ የተሰራን ቀለበት መንገድ መቋቋም አሁን ከስልጣንዎ ውጪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በቤቶች እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ የቤት ውስጥ አየር ጥራትን የሚያሻሽሉ መንገዶችን መፈለግ እንዲሁም በወደፊት የአካባቢ ውሳኔዎች ላይ ለማህበረሰብዎ ጥብቅና በመቆም የሰዎችን ኃይል መገንባት ይቻላል።*

**“ስለዚህ ምን” እንቅስቃሴ፡-**

1. በቀድሞ እንቅስቃሴ ውስጥ የተለየውን ፍላጎት ይመልከቱ (#1)። አሁን አንድ አጋርዎ "ግን ለምን?" እያለ እንዲጠይቅ ያድርጉ እና ለመመለስ ይሞክሩ። በተቻለ መጠን ግልጽ ይሁኑ - ለእርስዎ ግልጽ የሚመስለው ነገር ለሌላ ሰው ላይሆን ይችላል! *ለምሳሌ. "ከሌሎች ሰፈሮች ጋር ሲነፃፀር በአካባቢያችን ያሉ ልጆች በእጥፍ የሚሆኑት በአስም ይሰቃያሉ።"* ለእያንዳንዱ መልስ በይለጥፉት ማስታወሻ ላይ ይጻፉት። እነዚህ የዛፍዎ ሌሎች ቅርንጫፎች ናቸው።


2. ይህንን ለበርካታ ጊዜያት ይደጋግሙ። ወረቀትዎ እርስ በእርሳቸው የተገናኙበት በርካታ ቅርንጫፎች ያሉት ድር መምሰል መጀመር ይኖርበታል። መልሶችዎ ይበልጥ ትልቅ እና ሰፊ መሆን ሊጀምርይ ይችላሉ።

   *ለምሳሌ. “አስም ተጨማሪ የጤና ችግሮች ሊያስከትል ይችላል እና ከባድ ከሆነ በሆስፒታል መተኛትን ወይም ሞትን ሊያስከትል ይችላል" ወይም "አስም ያለባቸው ልጆች ከአስም ከሌለባቸው ልጆች አንጻር በበለጠ ብዙ ቀናትን ያቆማሉ፣ ይህም በትምህርታቸው ላይ ተጽእኖ ያሳድራል።”*

3. በወረቀቱ ላይ ሲመለከቱት እርምጃ ለመውሰድ የሚሆኑ በጣም ጠቃሚ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ይህ በተለምዶ በርካታ ነጥቦች ሊሆን ይችላል። እንዲሁም በሚያነጋግሩት ታዳሚ ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል። እነዚህ ላይ ያክብቡ እና ከአጋርዎ ጋር ውወያዩ።

   *ለምሳሌ. የሕዝብ ጤና ታዳሚዎች በልጆች ጤና ላይ ስላለው ተጽእኖ የበለጠ ሊያሳስባቸው ይችላል። የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች፣ አስተማሪዎች እና ሌሎች የትምህርት ታዳሚዎች በትምህርት ስላመለጡ ቀናት እና በመማር ላይ ስላላቸው ተጽእኖ ሊያሳስባቸው ይችላል። ወላጆች ስለሁለቱም ስጋት ሊያድርባቸው ይችላል፡፡*

**ምሳሌ፡- የአየር ብክለት እና አስም**




# የአመክንዮ ሞዴል


አሁን “ግን ለምን” እና “ስለዚህ ምን” የሚሉትን እንከልስ። ይህ በሥራዎ ምክንያት እንዲከሰቱ ስለሚፈልጓቸው ለውጦች እንዲያስቡ ያግዝዎታል። በአጭር ጊዜ፣ በመካከለኛ ጊዜ እና በረጅም ጊዜ ምን የተሻለ ሆኖ እንዲታይ ምን ይፈልጋሉ? *እነዚህን **ውጤቶች** እንሰይማቸው።*

የአመክንዮ ሞዴል ከተወሰኑ ተግባራት ስብስብ ጀምሮ እስከ ውጤቶቹ ድረስ ያለውን የፕሮጀክትዎን ፍሰት ያሳያል። እንዲሁም ሁሉም ሰው በፕሮጀክቱ ውጤቶች እና እንቅስቃሴዎች ላይ ግብአት እንዳለው ለማረጋገጥ ከቡድንዎ እና ከማህበረሰብዎ ጋር ውይይት ለመፍጠር ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። ከታች ያለው ሰንጠረዥ በፕሮጀክታችን ምክንያት ለመስራት ያቀድነውን (እንቅስቃሴ) እና ለማሻሻል ያቀድነውን (ውጤቶችን) ለማደራጀት ይረዳናል። ስለ እርስዎ ትልቅ የምስል ዕቅዶች ራስዎን ለማስታወስ ወደዚህ መመለስ ይችላሉ።

***የአመክንዮ ሞዴል***

| እንቅስቃሴዎች | ታዳሚ(ዎች) | የአጭር-ጊዜ ውጤቶች | የመካከለኛ-ጊዜ ውጤቶች | የረጅም ጊዜ ውጤቶች |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |




በመጀርሪያ በዚህ ሠንጠረዥ የቀኝ ክፍል ላይ እንጀምራለን (ውጤቶቹ)። ለማየት የምንፈልገውን ለውጥ የምንሰይመው እዚህ ነው። በዚህ ክፍለ-ጊዜ ውስጥ በውጤቶች ላይ ብቻ እናተኩራለን፣ ነገር ግን ወደዚያ በሚወስዱን የእንቅስቃሴዎች ዓይነቶች ላይ የተለየ ክፍለ-ጊዜ በኋላ ላይ ይኖረናል።

**በረዥም-ጊዜ ውጤት** እንጀምር። የመጨረሻ ግብዎ ምንድን ነው? መመልከት የሚፈልጉት ለውጥ ምንድን ነው? ይህ ወደፊት 5 ዓመታት ወይም 10 ዓመታት ማለት ሊሆን ይችላል። ምን ተሻሽሎ ወይም ተለውጦ ማየት እንደሚፈልጉ እንዲያስታውስዎት በእርስዎ “ግን ለምን” እና “ስለዚህ ምን” ላይ መለስ ብለው ይመልከቱ።*ለምሳሌ. ከአሰም ጋር የተያያዙ የተሻሻለ ክትትል እና የቀነሰ የመቅረት ጊዜ።*

በመቀጠል፣ ያንን የመጨረሻ፣ የረዥም ጊዜ ውጤት ለማግኘት ምን ዓይነት የመካከለኛ ጊዜ ለውጦችን ማየት ያስፈልግዎታል? *በ1፣ 3 ወይም 5 ዓመታት ውስጥ ማየት የሚፈልጉት ለውጥ ምንድን ነው?* እነዚህ **የመካከለኛ-ጊዜ ውጤቶች** ናቸው። *ለምሳሌ. ለአየር ብክለት ከመጋለጥ ጋር የተያያዙ የቀነሰ አስም፣ የማሳል እና ሌሎች የመተንፈሻ ምልክቶች።*

በመጨረሻም፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ውጤቶችን ለማሳካትሊመለከቷቸው የሚፈልጓቸው በ6 ወራት ውስጥ ወይም በአንድ ዓመት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ለውጦች - ይበልጥ ፈጣን ውጤቶች ምንድን ናቸው? እነዚህ **የአጭር-ጊዜ ውጤቶች** ይባላሉ። *ለምሳሌ. በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተጫኑ የHVAC ሥርዓቶች።*

በእርስዎ የአጭር፣ መካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ውጤቶች ላይ ከተስማሙ በኋላ፣ ወደ እነዚያ ውጤቶች እንዲደርሱዎት የሚያግዙዎትን **የእንቅስቃሴዎች** ዓይነቶችን መለየት መጀመር ይችላሉ።
ውጤቶቹን ለማሳካት በፕሮጀክትዎ ወቅት ተግባራቶቹን፣ አገልግሎቶቹን፣ ክንውኖችን ወይም ድርጊቶችን - እና በእነዚህ ለመድረስ ተስፋ ያደረጓቸውን ቡድኖች ይለዩ። እነዚህ ቀደም ባሉት ጊዜያት በእርስዎ ማህበረሰብ ውስጥ ወይም በሌሎች ማህበረሰቦች ውስጥ በተከናወኑ ተግባራት ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

እንዲሁም **የግምገማ** ርዕስን – እንቅስቃሴዎቹ ወደታቀዱት ውጤቶች እያንቀሳቀሱዎት እንደሆነ እንዴት ማወቅ እንደሚቻል የሚለውን ርዕስ እንመረምራለን።

***ግምገማ፦*** ውጤቶቹን እና ተግባራቶቹን ከሰየምን በኋላ የለየናቸው ተግባራት ውጤታማ መሆናቸውን እና ውጤቶቻችንን እየደረስን ስለመሆኑ እንዴት መወሰን እንዳለብን ማሰብ እንፈልጋለን። በመሠረቱ፣ እናደርጋለን ያልነውን እንደሠራን እንዴት እናውቃለን? **ቀደም ብለን እና ብዙ ጊዜ የምንገመግም ከሆነ ምን እየሰራ እንደሆነ እና እየሰራ እንዳልሆነ ማወቅ እና በአመክንዮ ሞዴላችን ላይ ለውጦችን ማድረግ እንችላለን።**

እድገትን ለመገምገም 'ለመለካት' ሊፈልጓቸው የሚችሏቸው ነገሮች፦
- የግንዛቤ እንቅስቃሴዎች ወይም በክስተቶች ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ብዛት
- በማህበረሰብ አባላት መካከል የአካባቢ ጉዳይ እውቀት መጨመር

***የአመክንዮ ሞዴል ምሳሌ***

| **እንቅስቃሴዎች** | **ታዳሚ(ዎች)** | **የአጭር-ጊዜ ውጤቶች** | **የመካከለኛ-ጊዜ ውጤቶች** | **የረጅም ጊዜ ውጤቶች** |
|---|---|---|---|---|
| *በከተማው ምክር ቤት ስብሰባ ወቅት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የHVAC ሥርዓቶችን ለመደገፍ የምስክርነት ቃል ያቅርቡ* | *የከተማ ምክር ቤት* | *በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተጫኑ የHVAC ሥርዓቶች* | *ለአየር ብክለት ከመጋለጥ ጋር የተያያዙ የቀነሰ አስም፣ የማሳል እና ሌሎች የመተንፈሻ ምልክቶች* | *ከአስም ጋር የተያያዙ የተሻሻለ ክትትል እና የቀነሰ የመቅረት ጊዜ።* |
| *በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ስላለው የአየር ጥራት ተደራሽነት እና የHVAC ሥርዓቶች ጥቅማጥቅሞች* | *በአጋሮች ትምህርት ቤቶች ላይ ያሉ መምህሮች* | | | |

ከላይ ባለው ምሳሌ ላይ በመመስረት፣ የሚከተሉትን ነገሮች ‘መለካት’ ልንፈልግ እንችላለን፡-

- ተደራሽነት የሆኑ የከተማ ምክር ቤት አባላት ብዛት
- ተደራሽ በሆኑ የአጋር ትምህርት ቤቶች ላይ ያሉ መምህሮች ብዛት
- የHVAC ሥርዓቶች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች ብዛት እና መቶኛ
- በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከአየር ብክለት የማጣራት ተጋላጭነት የመቶኛ መቀነስ
- የአስም የበሽታ ምልክቶችን ሪፖርት ያደረጉ ተማሪዎች እና ሰራተኛዎች
- የተጋላጭ ክስተቶች ብዛት

# ለቀጣይ እርምጃዎች የሚሆኑ መርጃዎች

UW CEHE ለእርስዎ እንደ መርጃ ሆኖ ሁልጊዜ እዚህ አለ። ከእኛ ጋር በአንድ ለአንድ መሰረት ለመገናኘት ከፈለጉ እባክዎ cehe@uw.edu ወይም 206-543-0608 ላይ ያነጋግሩን።

**የነፃ የአካባቢ ፍትህ ፈንድ ማድረግ ውሂብ ጎታዎች አገናኞች፡-**

- Northwest Environmental Justice Center (NWEJC)፡- https://nwejc.org/find-funding
    - ይህ የውሂብ ጎታ የግል፣ የግዛት፣ የጎሳ እና የፌዴራል ፈንድ ዕድሎችን በበAK፣ ID፣ OR፣ እና WA ውስጥ ላሉ የአካባቢያዊ የፍሕ ፕሮጀክቶች ያካትታል
- FundHubWA፡- https://fundhub.wa.gov/
    - ይህ የውሂብ ጎታ ስፖንሰር የሚደረገው እና የሚተዳደረው በዋሺንግተን ግዛት Department of Commerce እና የፌዴራል ፈንድ ዕድሎች በአየር ንብረት እና ንጹሕ ኢነርጂ National TCTAC Grant የውሂብ ጎታ ውስጥ ነው፡- https://www.ejtctac.org/grants
    - ይህ የውሂብ ጎታ የፌዴራል ፈንድ ዕድሎችን በሀገሪቱ ዙሪያ ላሉ የአካባቢያዊ ፍትሕ ፕሮጀክቶች ያካትታል
- የጎሳ ፈንድ መዝገብ፡- https://www.tribalfunding.org/
    - ይህ የውሂብ ጎታ ከHozhonigo Institute ሲሆን ለጎሳዎች እና የአካባቢ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የተነደፈ ነው

**ዕድሎችን ለማግኘት የሚሆኑ የሚቀላቀሏቸው ኢጋዥ የኢሜይል ዝርዝሮች እና መርጃዎች፡-**

- ለፌዴራል የፈንድ ዕድሎች፡-
    - Environmental Protection Network የፌዴራል ፈንድ ማድረግ ዕድሎች እና መመሪያ ባለሁለት-ሳምንታዊ ኢሜይል፡- https://www.environmentalprotectionnetwork.org/federal-funding-opportunities-guidance-updates/
    - Environmental Grantmakers Association የስጦታ ፈላጊዎች ንብረት ገጽ፡- https://ega.org/grant-seekers
- ለዋሺንግተን የግዛት ፈንድ ዕድሎች፡-
    - Department of Commerce ንጹህ ኃይል ሽልማቶች፡- ስለ የፈንድ ዕድሎች ለኢሜይል ዝማኔዎች ይመዝገቡ እና "የንጹሕ ኢነርጂ ሽልማቶች" ይምረጡ፡- https://public.govdelivery.com/accounts/WADOC/subscriber/new

# የግምገማ ፈንድ ማድረግ ማሳወቂያዎች መሣሪያ

ይህ መሣሪያ የተፈጠረው የፈንድ ማስታወቂያዎች ለድርጅትዎ ተስማሚ መሆን አለመሆናቸውን ለማየት እንዲረዳዎ ነው። ለአንድ ነገር ለማመልከት ከመወሰንዎ በፊት ከታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ያለውን መረጃ ይሰብስቡ እና በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ራስዎን ይጠይቁ። የሆነ ነገር ለድርጅትዎ ተስማሚ ሊሆን እንደሚችል ከወሰኑ ማመልከቻ ከማዘጋጀትዎ በፊት የማመልከቻዎች ጥያቄ ወይም የፈንድ ዕድል ማስታወቂያ በጥንቃቄ ማንበብዎን ያረጋግጡ።

| | | |
|---|---|---|
| **የፈንድ ዕድል ስም** | *ለምሳሌ. የHEAL Act የማህበረሰብ አቅም ስጦታ* | |
| **የገጽ አገናኝ** | [*https://doh.wa.gov/community-and-environment/health-equity/environmental-justice/grants/community-capacity*](https://doh.wa.gov/community-and-environment/health-equity/environmental-justice/grants/community-capacity) | |
| **መጠን** | *$250,000-500,000* | |
| **የጂዮግራፊ ትኩረት** | *የዋሺንግተን ግዛት* | |
| **ቀነ-ገደብ** | *ሜይ 5፣ 2024 በ 11:59 ከሰዓት ላይ* | |
| **የፈንድ ወቅት** | *የማስፈጸሚያ ቀን - ጁን 30፣ 2025* | |
| **የፈንድ ዓይነት** | *ግዛት* | |
| **ብቁ አመልካቾች** | *501(c)3 ደረጃ ያላቸው ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶች ለፕሮጀክት ፈንድ እንደ ብቸኛ ወይም መሪ አመልካች ለማመልከት ብቁ ናቸው እና የፊስካል ስፖንሰርሺፕ ካላቸው ድርጅቶች ጋር ሊተባበሩ ይችላሉ።* | |
| **የገንዘብ ቅድሚያ አሰጣጦች** | *ይህ የHEAL አቅም ስጦታ ፕሮግራም የአካባቢን ፍትህ (ኢጄ) ለማራመድ እና የአየር ንብረትን የመቋቋም አቅምን ለመገንባት በማህበረሰብ የሚመራ ውሳኔን በማሳደግ ላይ ያተኩራል።* | |
| **ብቁ እንቅስቃሴዎች** | የፕሮጀክት ስጦታ ፈንዶች የHEAL Act እንቅስቃሴዎች ውስጥ የማህበረሰብ አቅም ለመገንባት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። *ገንዘቦች መመሪያ እና ግብዓት ለማቅረብ አቅምን በመገንባት ላይ ያሉ እንቅስቃሴዎች ሊያካትቱ ይችላሉ ነገር ግን በእነዚህ አይገደቡም፡-*<br>- *በHEAL Act አፈጻጸም ላይ ያሉ ኤጀንሲዎች፣*<br>- *የአካባቢ ፍትህ ምክር ቤት የHEAL Actን አፈፃፀም እና*<br>- *የጤና ጥበቃ መምሪያ ስለ የአካባቢ ጤና ልዩነቶች ካርታ ማሻሻያ።* | |

| | | |
|---|---|---|
| **የፈቃድ ደብዳቤ ያስፈልጋል?** | *አይ* | |
| **ተዛማጅ ፈንዶች ያስፈልጋል?** | *አይ* | |

የፈንድ ማሳወቂያን ከገመገሙ በኋላ ራስዎን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፡-

1. የእኔ ድርጅት **ለማመልከት ብቁ ነው?**
2. የፕሮጀክት ሀሳቤ **ከፈንድ ቅድሚያ አሰጣጦች** ጋር ይስማማል?
3. የፕሮጀክት ሀሳቤ **ብቁ እንቅስቃሴዎች** ጋር ይስማማል?
4. ማመልከቻ ለማዘጋጀት ወይም የፈቃድ ደብዳቤ ለማቅረብ **ከቀነ ገደቡ** በፊት ምን ያህል ጊዜ አለኝ?
5. ድርጅቴ ፕሮጀክቱን **የፈንድ ጊዜ** የማጠናቀቅ አቅም አለው?
6. የእኔ ድርጅት ይህን **የፈንድ ዓይነትን** ለማስተዳደር አቅም አለው?
7. ተዛማጅ ገንዘቦች የሚያስፈልግ ከሆነ፣ የእኔ ድርጅት **ተዛማጅ ፈንዶች** አለው?
8. የእኔ ድርጅት ለዚህ **የፈንድ ዓይነት** አመልክቶ ያውቃል? መለያ ማዘጋጀት ወይም ለማንኛውም ነገር መመዝገብ አለብኝ? (ለምሳሌ. Sam.gov ለፌዴራል፣ Statewide Vendor Number ለዋሺንግተን ግዛት፣ etc.)

ከላይ ላሉት ጥያቄዎች **አዎ** ብለው ከመለሱ የመሳካት ዕድሉ ሰፊ ነው! ከዚህ ሆነው፣ የፈቃድ ደብዳቤ ወይም ማመልከቻ ከማስገባትዎ በፊት Applications for Notice (የማመልከቻዎች ጥያቄዎች) ወይም Notice of Funding Opportunity (የፈንድ ዕድል ማስታወቂያን) ጥያቄ በጥንቃቄ ማንበብ አስፈላጊ ነው።

# ስለ UW CEHE

University of Washington Center for Environmental Health Equity (UW CEHE, (የዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጤና ፍትሃዊነት ማዕከል) በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶችን፣ የጎሳ ድርጅቶችን እና ጎሳዎችን የሚያገለግል የአካባቢ ጤና ቴክኒካል ድጋፍ ማዕከል ነው።

UW CEHE በአላስካ፣ አይዳሆ፣ ኦሪገን እና ዋሽንግተን ላሉ ቡድኖች የአካባቢ እና የኢነርጂ ፍትህ ቴክኒካል ድጋፍ ለመስጠት በUnited States Environmental Protection Agency (US EPA, የዩናይትድ ስቴትስ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ) እና Department Of Environment (DOE, የአካባቢ ጥበቃ መምሪያ) የሚደገፈው እንደ አዲስ Thriving Communities Technical Assistance Center (TCTAC, የበለጸጉ ማህበረሰቦች የቴክኒክ ድጋፍ ማዕከል) ሆኖ በጁን 1፣ 2023 ተጀመረ። ከ400 በላይ የቴክኒካል ድጋፍ ጉዳዮችን በማገልገል ከግማሽ በላይ በሆነ ፈንድ ገጠር እና ራቅ ያሉ ማህበረሰቦችን በማገልገል ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶችን ከ32 ሚሊዮን ዶላር በላይ ለሥራቸው የሚሆን ፈንድ እንዲሰበስቡ ከረዳ በኋላ ለTCTAC ፕሮግራም የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ በፌዴራል ቅድሚያ በሚሰጣቸው ለውጦች ምክንያት በሜይ 2 ቀን 2025 በድንገት እና ያለጊዜው ተቋርጧል። በእነዚህ ለውጦች ምክንያት፣ የእኛ ማዕከል አሁን በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ ላሉ ማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶች፣ የጎሳ ድርጅቶች እና ጎሳዎች የአካባቢ ጤና የስጦታ ጽሑፍ ዕርዳታን በማገልገል ላይ ያተኩራል።

በተጨማሪም፣ በፖርትላንድ፣ ኦሬጎን ላይ ከሚገኘው ሌላ TCTAC Northwest Environmental Justice Center ጋር አብረን እንሰራለን። ስለ ስራቸው እና የአሁን ሁኔታቸው እዚህ ተጨማሪ መረጃን ማግኘት ይችላሉ፡- https://nwejc.org

ስለ UW CEHE የበለጠ ለማወቅ የእኛን ድር ጣቢያ deohs.washington.edu/cehe/ ላይ ይጎብኙ ወይም cehe@uw.edu ወይም 206-543-0608 ላይ ከእኛ ጋር ይገናኙ።